የአይሪሽ ድንች ምርምርና ልማት ማህበር

መተዳደሪያ ደንብ

መስከረም 2015 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አንቀጽ 1፡ <u>መቋቋም</u>

"የአይሪሽ ድንች ምርምርና ልማት ማህበር " የተባለ በ መጋቢት 08 ቀን/2014 ዓ/ም ተቋቁሟል::

አንቀጽ 2፡ <u>ስያሜ</u>

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ***የአይሪሽ ድንች ምርምርና ልማት ማህበር*** በሚል ስም የሚጠራ ሲሆን ከዚህ በኋላ " ማህበር" ተብሎ ይጠቀሳል::

አንቀጽ 3፡ <u>የመስራቾች ዝርዝር</u>

ተ.ቁ	ሙሉ ስም	አድራሻ/ወረዳ ክፍለከተማ የቤት ቁጥር	ዜግነት
1	ዶ/ር አፀደ ሰለሞን ረታ	አ/አ፣ 06፣ ኮ/ቀራንዮ	ኢትዮጵያዊ
2	ዶ/ር እስመለአለም ምህረቱ ተገኝ	ባህርዳር፣ አ/አ፣ ዳ/ምኒልክ፣ 545	ኢትዮጵያዊ
3	አቶ አስፋው መኩሪያ ይርጉ	አ/አ፣ 03፣ ለሚኩራ፣ አዲስ	ኢትዮጵያዊ
4	አቶ አፈወርቅ በዳዊ ሐሰን	ኦሮሚያ፣ ምስራቅ ሸዋ፣ ቢሾፍቱ	ኢትዮጵያዊ
5	ዶ/ር ሰጠኝ ገበየሁ አንድሬ	ኦሮሚያ፣ መልካ ገፈርሳ፣ ቡራዩ	ኢትዮጵያዊ
6	ወ/ሮ ማህሌት ዮሐንስ ስርጋዊ	አ/አ፣ 04፣ ቦሌ፣ 039	ኢትዮጵያዊ
7	አቶ ደርበው ከበደ አልማዝ	አ/አ፣ 02፣ ኮ/ቀራንዮ	ኢትዮጵያዊ
8	አቶ ሞገስ ጎበና ጅሩ	አ/አ፣ 04፣ የካ፣ 327	ኢትዮጵያዊ
9	ወ/ሮ ራውዳ ሰማን ጁቤር	አ/አ፣ 07፣ አራዳ፣ 731	ኢትዮጵያዊ

አንቀጽ 4፡ <u>ዓላማ</u>

የማህበሩ አላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1) በአሁን ጊዜ በኢትዮጵያ በርካታ ባለድርሻ አካላት በድንች ምርምር እና ልማት የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛሉ:: ሆኖም እነዚህ አካላት በተበታተነ መልኩ የሚሰሩ ስለሆኑ የሚጠበቀው አመርቂ ውጤት አልተገኘም:: በመሆኑም ይህንን የድንች ሴክተር ውጤታማ ለማድረግ እና ምርትና ምርታማነትን ለመጨመር የዝቅተኛ ገቢ አርሶ አደሮችን፣ የንግድ ድርጅቶች፣ አነስተኛ አቀነባባሪዎች እና በተለይም ለችግር ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን (ሴቶችና ወጣቶችን) በተቀናጀ መልኩ በድንች አቅርቦት ተጠቃሚና ውጤታማ ለማድረግ ይህ ማህበር ጉልህ ሚና አለው::

2) የጋራ የሆነ ፕሮግራም፣ ክትትልና ግምገማ ማዕቀፍ ማዘጋጀት፣

3) በድንች ምርምርና ልማት ትግበራ ላይ ለማህበሩ አባላት ድጋፍ ማድረግ፣

4) መረጃ እና እውቀትን መሰረት ያደረገ በድንች ላይ የምርምርና ልማት ስራዎችን ውጤታማ ለማድረግ መረጃዎችን፣ እውቀቶችን እና መልካም ተሞክሮዎችን ማሰባሰብና ማደራጀት፣

5) በድንች ምርምርና ልማት ዙሪያ ያሉ የቴክኖሎጂ፣ የአሰራርና የገበያ መረጃዎችን መሰብሰብ፣ ማደራጀት፣ መተንተንና ለተጠቃሚ ተደራሽ ማድረግ።

6) ማህበሩ የገንዘብና የሌሎች ድጋፎችን እንዲያገኝ ማስቻል።

7) በአለም አቀፍ ለጋሾች ዘንድ ድንችን የልማት አጀንዳ ሆኖ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታውን ማስተዋወቅ፣

8) መልካም ተሞክሮዎችን ማስፋፋት፤

9) የእውቅት እና የክህሎት ሽግግርን ማመቻቸት፣

10) የምርምርና የልማት ስራዎች የአርሶ አደሩን እና ሌሎች ተጠቃሚዎችን ፍላጎት መሰረት ያደረጉ /ያካተቱ/ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤

11) በአገራችን የሚወጡ የግብርና ልማት ፖሊሲዎች እና እቅዶች ለድንች ልማት እና ምርምር ተገቢውን ትኩረት እንዲሰጡ ጥረት ማድረግ፤

አንቀጽ 5፡ <u>የበጀት አመት</u>

የማኅበሩ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1 እስከ ሰኔ 30 ይሆናል።

አንቀጽ 6፡ <u>ትርጉም</u>

1. **"ማህበር"** ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የተቋቋመው ***"የአይሪሽ ድንች ምርምርና ልማት ማህበር"*** ነው።
2. **"የአይሪሽ ድንች"** በተለምዶ ድቡልቡል ድንች ወይንም ድንች ብለን የምንጠራው አትክልት ነው።
3. **"ባለሥልጣን"** ማለት በአዋጅ ቁጥር 1113/2011 ንዑስ አንቀጽ 4 እና የፌደራል መንግስት የአስፈጻሚ አካላትን ሥልጣን ተግባር ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሰረት የተቋቋመው የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ነው።

4. “ጠቅላላ ጉባኤ” ማለት መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማህበሩ የበላይ አካል ነው፡

5. *አዋጅ ማለት የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር 1113/2011 ነው።*

አንቀጽ 7፡ ***<u>መደበኛ አባላት</u>***

1. መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በጠቅላላው ጉባኤ ውሣኔ ተቀባይነት ያገኙ አባላትን ይይዛል።
2. የሚከተሉትን መመዘኛዎች የሚያሟላ/የምታሟላ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ሰው መደበኛ አባል መሆን ይችላል/ትችላለች።
   ሀ. በማህበሩ አላማና ግብ የሚያምን/የምታምን፤
   ለ. ዕድሜው/ዋ ከ18 ዓመትና በላይ የሆነ/ች፣
   ሐ. የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባኤው በየጊዜው የሚወጡ የሥነ-ምግባር ደንቦችን የሚቀበል/የምትቀበልና ተግባራዊ የሚያደርግ/የምታደርግ፣
   መ. በአባላት ጠቅላላ ጉባኤ በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች መክፈል የሚችል/የምትችል፣
   ሠ. በህግ መብቱ/ቷ ያልተገፈፈ/ች፣

አንቀጽ 8፡ <u>የክብር አባላት</u>

1. የማህበሩ አባል ያልሆኑና የማህበሩን አላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ ፤ ማህበሩ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በማህበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኙ ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ፡ ፡
2. የክብር አባላት በማህበሩ ውስጥ የመምረጥ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም።
3. የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት ካልሆነ በቀር የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን የመክፈል ግዴታ አይኖርባቸውም።

አንቀጽ 9፡ <u>የአባላት መብት</u>

1. ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው፣
2. የማህበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ሰው የማይተላለፍ የግል መብት ነው።
3. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል፦
   ሀ. ለማህበሩ ዓላማና ተልእኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ማናቸውንም አይነት ስራዎች የመስራት፣
   ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለማህበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣
   ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለማህበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምጽ የመስጠት መብት አለው/አላት።
   መ. ማንኛውም የማህበሩ መደበኛ አባል አባልነቱ ንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በስራ አስፈጻሚ የመሰማት መብት አለው።

አንቀጽ 10፡ <u>የአባላት ግዴታ</u>

1. ማንኛውም አባል የአባልነት መዋጮውን በወቅቱ መክፈል አለበት/አለባት፣
2. አንድ አባል ከአባልነት ከመሰናበቱ/ቷ በፊት የሚፈለግበትን /የሚፈለግባትን ዕዳ መክፈል ይኖርበታል/ይኖርባታል፣
3. ማንኛውም አባል የማህበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣በጠቅላላ ጉባኤ የሚወጡ መመሪያዎችና ውሣኔዎችን ማክበር አለበት/አለባት፣
4. ማንኛውም አባል የማህበሩን ዓላማና የገባቸውን/የገባባቸውን ግዴታዎች ማክበር፣ የማህበሩን ንብረት የመንከባከብና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት/አለባት፣
5. በማህበሩ መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት/አለባት:

አንቀጽ 11፡ <u>የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች</u>

1. ድርጅቶች በዓመት 6000.00 (ስድስት ሺህ ብር) ሲያዋጡ የአርሶ አደር ማህበራት ደግሞ 3000.00 (ሶስት ሺህ ብር) ያዋጣሉ።

2. በጠቅላላ ጉባኤው በሚወሰነው የጊዜ ገደብ የማይከፍል/የማትከፍል ሰው በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ መሰረት መቀጮ ይጣልበታል/ይጣልባታል።
3. የአባልነት መዋጮ ባለመክፈሉ/ሏ ምክንያት በጠቅላላ ጉባኤው የተጣለበትን/የተጣለባትን ቅጣት ያልከፈለ/ች አባል ላይ እዳውን/እዳዋን እስኪከፍል/እስክትከፍል ድረስ ጠቅላላ ጉባኤው ድምፅ የመስጠት ወይም ማንኛውንም ሌላ መብት ሊያነሳ ይችላል::

አንቀጽ 12፡ <u>አባልነት ሰለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች</u>


አንድ የማህበሩ አባል አባልነቱ/ቷ የሚቋረጠው፣

1. ሲሞት/ስትሞት፣
2. መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሠረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት/እንድትሰናበት ጠቅላላ ጉባኤው ሲወስን፣
3. የማህበሩን ክብርና ህልውና በሚነካ ወይም በሚያናጋ ተግባር ላይ መሳተፉ/ፏ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
4. ለማህበሩ ዓላማ መሣካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሣትፎ ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን/ሳትሆን ሲቀር/ስትቀር እና ይኸውም በጠቅላላ ጉባኤው ሲወሰን፣
5. መዋጮውን ለአንድ አመት ያህል ጊዜ ባለመክፈሉ/ሏ በጠቅላላ ጉባኤው ከአባልነቱ/ቷ ሲሰናበት/ስትሰናበት፣
6. ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታው/ዋን ወይም መብቱን/ዋን ሲነጠቅ/ስትነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ/ስትወገድ፣
7. ከማህበሩ አባልነት በራሱ/ሷ ፍቃድ ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ/ስትጠይቅ ይሆናል፣

አንቀጽ 13፡ <u>የማህበሩ አደረጃጀት</u>

1. ማህበሩ የሚከተሉት የአመራር አካላት ይኖሩታል::
   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ
   ለ. ኦዲተር
   ሐ. ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ እና
   መ. ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል::

2. ማህበሩ በሚከተለው መልኩ የተዋቀረ ነው:-



3. የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል የሆነ ማናቸውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ሆኖ ሊሰራ አይችልም።

አንቀጽ 14፡ <u>የጠቅላላ ጉባኤው ስልጣንና ተግባር</u>

1. ጠቅላላ ጉባኤው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 5 ላይ የተጠቀሱትን መደበኛ አባላት የሚያካትት ሆኖ በህግና በማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል:-
   ሀ. ጠቅላላ ጉባኤው የማህበሩ የበላይ አካል ነው፣
   ለ. የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ ያወጣል፣ ያሻሽላል፣
   ሐ. በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት የማህበሩን ኦዲተር ይመርጣል፣ ያሰናብታል፣ክፍያውን ይወስናል፣
   መ. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላትን፣ የጉባኤውን ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ ይሾማል ፣ ይሽራል፣
   ሠ. የማህበሩን ዋና መስሪያ ቤት የመለወጥና ቅርንጫፎች የመክፈት የመጨረሻ ውሳኔ ያሳልፋል፣
   ረ. ማህበሩን ማፍረስና ንብረት ማጣራት ላይ ይወስናል፣
   ሰ. የማህበሩን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት፣ የሂሳብ መግለጫ፣ የኦዲት ሪፖርትና ዓመታዊ በጀት ያፀድቃል፣
   ሸ. ዓመታዊ የስራ ፕሮግራምን በመመርመር እቅድና በጀት ያፀድቃል፣
   ቀ. በማህበሩ የፖሊሲና የስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ ይወስናል፣
   በ. የማህበሩ አባል ለመሆን በቀረበው ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፣
   ተ. በዚህ መተዳደሪያ ደንብ አንቀፅ 9 በተገለፀው መሠረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ከአባልነት እንዲሰረዝ ይወስናል፣

ቸ. የአባላት መዋጮ ሌሎች ክፍያዎችንና የቅጣት መጠን ላይ ይወስናል፣

ኀ. የማህበሩ ሂሳብ በውጭ ኦዲተር እንዲመረመር ያደርጋል፣

ነ. የጠቅላላ ጉባኤውን የስብሰባ ሥነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል፣

ኘ. ማህበሩ ከሌሎች ማህበራት ጋር ህብረት ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም የመከፈል ወይም የመለወጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሠጣል፣

አ. በማህበሩ ሌሎች አካላት ስልጣንና ተግባራት ስር በማይወድቁ ማህበሩን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ይወስናል::

2. ጠቅላላ ጉባኤው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በዚህ አንቀጽ ንዑስ-አንቀጽ 1 (ሠ)፣ (በ)፣ (ቸ) እና (ኀ) መሰረት የተሰጡትን ስልጣንና ተግባራት ለማህበሩ አካላት ወይም ለሚያቋቁመው ቋሚ ወይም ጊዜያዊ ኮሚቴ በውክልና ማስተላለፍ ይችላል::

3. ጠቅላላ ጉባኤው ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ህግጋት ጋር ግጭት ከሌለው በስተቀር በዚህ መተዳደሪያ ደንብ ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል::

አንቀጽ 15: <u>የጠቅላላ ጉባኤ ድምጽ አሰጣጥ</u>

1. ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ/ታ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው/የምትሰጠው ድምጽ አንድ ብቻ ይሆናል::
2. ማንኛውም የማህበር አባላት እኩል ድምጽ አላቸው::
3. ጠቅላላ ጉባኤው በግልጽ ካልፈቀደ በስተቀር ማንኛውም አባል በስብሰባ ላይ እራሱ/ሷ ተገኝቶ/ታ ድምጽ መስጠት ይኖርበታል/ባታል::
4. የድምጽ አሰጣጡ ሥነ-ሥርዓት ፍትሀዊ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል::
5. ከጠቅላላው ጉባኤ የተለየ ሃሣብ ያለው/ያላት የማህበር አባል የልዩነት ሀሣቡን/ቧን በቃለ ጉብኤው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል/ትችላለች::
6. ማንኛውም መደበኛ የማህበር አባል በጠቅላላ ጉባኤው የተላለፈው ውሣኔ የሃገሪቱን ህግጋት ወይም የማህበሩን መተዳደሪያ ደንብ

ይጥሳል ብሎ/ላ ሲያምን/ስታምን ለባለሥልጣን መ/ቤት ሊያመለክት/ልታመለክት ይችላል/ትችላለች::

አንቀጽ 16: <u>የጠቅላላ ጉባኤው አመራር አካላት ስልጣንና ተግባራት</u>

ጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢ እና ፀሐፊ የሚኖረው ሲሆን ስልጣንና ተግባራቸውም የሚከተለው ነው፣

1. **የጠቅላላ ጉባዔ ሰብሳቢ፣**
   ሀ. የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባዎች ይጠራል/ትጠራለች ከጸሀፊው/ዋ ጋር በመሆን አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ታዘጋጃለች
   ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል/ትመራለች፣
   ሐ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚያወጣቸውን ደንቦችና የሚሰጣቸውን ውሣኔዎች በትክክል ስራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል/ትከታተላለች፣
   መ. ጉባኤው ያጸደቃቸው ዓመታዊ የሥራ ክንውን፣ የሥራና የአዲት ሪፖርቶችና የሂሳብ መግለጫ ለሚመለከታቸው መንግሥታዊ አካላት እና እንደአስፈላጊነቱ ለተጠቃሚዎችና ለለጋሾች እንዲደርሱ ያደርጋል/ታደርጋለች፣
   ሠ. ለጉባኤው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ ለፀሐፊው በአጀንዳነት ያስይዛል፣
2. **ምክትል ሰብሳቢ**
   ሀ. ስበሳቢው/ዋ በማይኖርበት/በማትኖርበት ጊዜ ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሰራለች፣
   ለ. በሰብሳቢው/ዋ ወይም በጠቅላላ ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ሰራዎች ያከናውናል/ታከናውናለች፣
3. **ፀሐፊ**
   ሀ.ከሰብሳቢው/ዋጋርበመሆን ለጉባኤው አጀንዳዎችን ያዘጋጃል/ ታዘጋጃለች፣
   ለ. የጉባኤውን ስብሰባ ቃለ ጉብኤ ይይዛል/ትይዛለች፣

አንቀጽ 17: <u>የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ</u>

1. የጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሊቀመንበር ጠሪነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት ሊቀመንበሩ በ30 ቀናት ውስጥ ስብሰባ ያልጠራ እንደሆን ባለሥልጣን መ/ቤቱ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት በሊቀመንበሩ አማካኝነት ወይም በራሱ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሰባ ሊጠራ ይችላል።
3. የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ የተጠራው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከሆነ ባለሥልጣን መ/ቤቱ የጠቅላላ ጉባኤ ሊቀመንበር የሚሆን/የምትሆን ሰው ለምርጫ ሊያቀርብ ይችላል።
4. የማህበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በፕሬዝዳንቱ ወይም ሊቀመንበሩ ከማህበሩ 10 ከመቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፤
5. ለጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ አስራ አምስት የስራ ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከአምስት የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ቀኑን፤ ጊዜውን እንዲያውቁት ይደረጋል።
6. የማህበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል።
7. ከላይ በአንቀጽ 6 የተደነገገው እንዳለ ሆኖ ምልዓተ ጉባኤው ለሁለት ተከታታይ ስብሰባዎች ካልተሟላ የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ያደርጋል/ታደርጋለች።
8. በጠቅላላ ጉባኤው መደበኛ ስብሰባ ላይ የተለያዩ ጉዳዮች እንደየሁኔታው በአጀንዳነት ተይዘው ለውይይት ይቀርባሉ ፣ማንኛውም ጉዳይ በአጀንዳ እንዲያዝለት የሚፈልግ አባል ጠቅላላ ጉባኤ ከመሰብሰቡ ቢያንስ ከአንድ ሳምንት በፊት ለጉባኤው ፀሐፊ/ፕሬዘዳንቱ/የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ/ በጽሁፍ ይህንኑ ማስታወቅ ይኖርበታል/ይኖርባታል።

አንቀጽ 18፡ <u>የምርጫና የውሣኔ አሰጣጥ ሥነሥርዓት</u>

1. ማህበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፣

2. ጉባዔው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፣
3. አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባኤው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፣
4. ጠቅላላ ጉባዔው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች የተጓደሉ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላትን ለመተካት እንደ አስፈላጊነቱ የአስመራጭ ኮሚቴ ያቋቁማል፣
5. የምርጫ ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ተመራጮች በድጋሚ እንዲያገለግሉ ከተፈለገ በጥቆማ ለውድድር ቀርበው በድምጽ ብልጫ መመረጥ ይኖርባቸዋል፣ ሆኖም ለ3 ኛ ጊዜ ለመመረጥ አንድ የምርጫ ዘመን /4 ዓመት/ መቆየት ይኖርባቸዋል።
6. የጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምጽ እኩል ሲሆን ሊቀመንበሩ ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
7. የማህበሩ የሰብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆዎችን የተከተለ መሆን አለበት፣
8. የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም፤ ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባኤው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፣
9. አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ስራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፣
10. የቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሠናበቱበት ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ስራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፣
11. በጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳነት ቀርበው ያጸደቁ ናያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሣኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፣

አንቀጽ 20፡ <u>የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ሥልጣንና ተግባራት</u>

1. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በጠቅላላ ጉባዔው የሚቋቋምና ተጠሪነቱም ለዚሁ አካል
   ሆኖ የማህበሩን የእለት ተእለት ሥራ ያከናውናል።
2. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

ሀ. የማህበሩን ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት በጀት ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ
እንዲጸድቅ ያደርጋል፣

ለ. የማህበሩን ዓመታዊ የሥራ መርሀ ግብርና የአጭር፣ የመካከለኛና የረዥም ጊዜ
እቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ አንዲጸድቅ ያደርጋል፣

ሐ. የማህበሩን ዓላማዎች ለማስፈጸም የገቢ ምንጮችን የገንዘብ ፣
የጉልበት ወይም የማቴሪያል ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ያፈላልጋል፣

መ. የማህበሩን ፖሊሲ በማመንጨት ያቀርባል፣

ሠ. ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣
ዝውውር፣ እድገት፣ ስንብት፣ ደመወዝና አበል ይወስናል።

ረ. ጠቅላላ ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎች በተግባር ላይ እንዲውሉ
ያደርጋል።

ሰ. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች አስፈላጊ በሆኑ ቦታዎች እንዲከፈቱ ለጠቅላላ
ጉባኤው አቅርቦ ያስወስናል።

ሸ. የአባልነት ግዴታቸውን ያልተወጡ አባላት እንዲሰረዙ ለጠቅላላ
ጉባኤው የውሳኔ ሐሳብ ያቀርባል።

ቀ. የራሱን የአሰራር ስነ ስርዓት ያወጣል።

በ. በጠቅላላ ጉባዔው የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

ተ. የማህበሩን መደበኛና አስቸኳይ ስብሰባዎች ይጠራል።

አንቀጽ 21: <u>የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላ ት</u>

1. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፦

ሀ. ኘሬዝዳንት

ለ. ምክትል ኘሬዝዳንት

ሐ. ፀሐፊ

መ. ሂሣብ ሹም

ሠ. ገንዘብ ያዥ፤ እና

ረ. ሌሎች ሁለት አባላት ይኖሩታል።

3. **የማህበሩ ኘሬዝዳንቱ/ቷ ስልጣንና ተግባር፤**

በጠቅላላ ጉባኤው የሚመረጥ ሲሆን የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡

ሀ. ጠቅላላ ጉባኤ የሚያቋቁማቸውን የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴዎችን በሊቀ መንበርነት ይመራል፡፡

ለ. ማህበሩን በሶስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡

ሐ. በማህበሩ ሥም የተከፈተውን የባንክ ሒሳብ ቼኮችንና የወጪ ስነዶችን ከሒሳብ ሹሙ ጋር በመሆን በጣምራ ይፈርማል፡፡

መ. ለማህበሩ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ይፈቅዳል፡፡

ሠ. የ3ወር፣ የ6ወር ናዓመታዊ የሥራ፣የፋይናንስ ሪፖርቶችን እያዘጋጀ ለሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ያቀርባል፡፡

ረ. በማህበሩ ሥም ደብዳቤዎችን ይፈርማል፡፡

ሰ. ሂሳብ ሹምና ገንዘብ ያዡን ጨምሮ በሥሩ የሚገኙትን ሠራተኞች እያስተባበረ እየተከታተለና እየተቆጣጠረ የማህበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ እንቅስቃሴ ይመራል፡፡

ሸ. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴውን በማስፈቀድ በማህበሩ ሥም ንብረት ለመግዛትና ለመሸጥ የሚያስችሉ ውሎችን ይዋዋላል፡፡

ቀ. በጠቅላላው ጉባኤው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በተግባር ላይ ያውላሉ፡፡

በ. ሌሎች ለሥራ አስፈፃሚው የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል፡፡

4.ምክትል ኘሬዝዳንቱ/ቷ፤

ሀ. ኘሬዝዳንቱ/ቷ በማይኖሩበት ጊዜ ኘሬዝዳንቱን/ቷን ተክቶ/ታ ይሠራል/ትሰራለች፡፡

ለ. በፕሬዝዳንቱ ወይም በጠቅላላ ጉባዔው የሚሰጡ ተጨማሪ ስራዎችን ያከናውናል፡፡

5.ፀሐፊው/ዋ

ሀ. የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ ፀሐፊ ሆኖ ያገለግላል፡፡

ለ. ከሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በሚሰጠው ትዕዛዝ መሠረት የማህበሩን የመፃፍ ግንኙነት ሥራዎች ያከናውናል፡፡

ሐ. የሥራ አስፈፃሚውን አጀንዳ ያዘጋጃል፣ ቃለ ጉባኤ ይይዛል፡፡

መ. የማህበሩን ማህተም፣ሰነድና መዛግብት ይይዛል፡፡

ሠ. የአባልነት ማመልከቻዎችን ይቀበላል፡፡

6.ሒሳብ ሹም

ሀ. የማህበሩን ገቢና ወጪ ሂሳብ በበላይነት ይቆጣጠራል:

ለ. የማህበሩ ሂሳብ የሚንቀሳቀሰው በታወቀ የሂሳብ አሠራር ደንብ መሠረት መሆኑን ያረጋግጣል::

ሐ. በማህበሩ ሥም የተከፈተውን የባንክ ሂሳብ ቼክና የወጪ ሰነዶች ላይ ከኘሬዝዳንቱ ጋር በጣምራ ይፈርማል::

መ. የማህበሩ የሂሳብ መዛግብት በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል::

ሠ. የሂሳብ መዝገብ፣ ገቢና ወጭ፣ ኃብትና እዳን ያካተተ ሰነድ ያዘጋጃል::

ረ. ማህበሩ ገቢ በሚያስገኙ ሥራዎች ላይ በሚሰማራበት ጊዜ ለዚሁ ሥራ የሚውሉ የተለያዩ የሂሳብ መዛግብት እንዲያዙ ያደርጋል::

7. **የማሕበሩ ገንዘብ ያዥ፣**

ሀ. የማህበሩን ገቢዎች በህጋዊ ደረሰኝ ይሰበስባል::

ለ. የተሰበሰበውን ገንዘብ አገር ውስጥ በሚገኝ ባንክ ገቢ ያደርጋል ገቢ ያደረገበትን ደረሰኝ በጥንቃቄ ያስቀምጣል፣

ሐ. ለሥራ ማስኬጃና ለማህበሩ ጥቃቅን ወጪዎች የሚሆን ከብር 10,000.00 (አስር ሺህ ብር) ያልበለጠ ገንዘብ ይይዛል::

መ. ከሒሳብ ሹሙ ጋር የወጪና የገቢ ሒሳብ በየወሩ ያመሳክራል::

ሠ. የማህበሩን ቼክ ይይዛል::

ረ. በጣምራ ፊርማ በሒሳብ ሹሙና በኘሬዝዳንቱ በወጪ ሰነድ ሲታዘዝ ወጪ ያደርጋል::

አንቀጽ 22:- <u>የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የስብሰባ፣ የድምጽ አሰጣጥ ሥነ-ሥርዓት የአባላት የአገልግሎት ዘመን</u>

1. የኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በዓመት አራት ጊዜ የሚከ ወን ሆ አስቸኳይ ስብሰባ የሚያስፈልግበት ምክንያት ሲ ር ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፣
2. አስቸኳይ ስብሰባ በፕሬዝዳንቱ ወይም ምክትል ፕሬዝዳንቱ ሊጠራ ይችላል፣
3. ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ-ጉባዔ ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል። በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባኤ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፣
4. ውሣኔዎች በድምፅ ብልጫ ይተላለፋሉ፤ ድምፅ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ፕሬዝዳንቱ የደገፈው ሃሳብ ይፀ ል፣

5. የኮሚቴ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለአራት ዓመት ይሆ ል። ሆ ም አን ድ የኮሚቴ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ ሊመረጥ አይችልም ፣
6. የኮሚቴ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ ሆኖም ለማህበሩ ስራ ለሚያወጡት ወጪዎች ማካካሻ ይከፈላል ።

አንቀጽ 23: <u>የኦዲተር ኃላፊነት ተግባር</u>

1. የማኅበሩ ኦዲተር የማህበሩ ፕሬዝዳንት ወይም የሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባል ሊሆን አይችልም።
2. ኦዲተሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላላው ጉባዔ ሆኖ ፤ የሚከተሉት ሥልጣን ተግባሮች ይኖሩታል፤
3. የማኅበሩን የገንዘብ የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣
4. የማኅበሩ የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣
5. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሰረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፤

አን ቀጽ 24: <u>የማኅበሩ የገቢ ምንጭ</u>

የማኅበሩ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን በጠቅላላ ጉባኤው ውሳኔ ከሕዝባዊ መዋጮ፣ ከገቢ ማስገኛ ስራዎችና ከእርዳታ ሰጪዎች የሚገኝ ገን ዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል።

አን ቀጽ 25: <u>የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል</u>

1. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ ከጠቅላላ ጉባኤው አባላት ¼ ኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል።
2. የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባኤ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለጠቅላላ ጉባኤው ስብሳቢ ፣ ጸሀፊ ወይም ፕሬዝዳንት የጉባኤው ጥሪ ከመሰራጨቱ በፊት መቅረብ ይኖርበታል።
3. የመተዳደሪያ ደንቡ የሚሻሻለው የማሻሻያ ሀሳቡ ከግማሽ በላይ አባላት በተገኙበት የጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ 3/4ኛ ድምጽ ሲያገኝ ነው።

4. የመተዳደሪያ ደንቡ እንዲሻሻል የተላለፈውን ውሳኔ ባለሥልጣን መ/ቤቱ ያላጸደቀው እንደሆን ባልጸደቀበት ምክንያት ላይ የሚወያይ ስብሰባ ይቀጠራል።
5. እንዲሻሻል የተወሰነው የመተዳደሪያ ደንብ በባለሥልጣን መ/ቤቱ በኩል ታይቶ ከመጽደቁ በፊት ስራ ላይ ሊውል አይችልም።

አቀን ጽ 26: <u>ስለማህበሩ መዋሃድና መለወጥ</u>

1. ማህበሩ ወደተለያዩ ማህበራት የሚከፋፈለው፣ ከሌላ ማህበር ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ በጎ አድራጎት ድርጅትነት የሚለወጠው በጠቅላላ ጉባኤው በ3/4ኛ ድምፅ ሲወስን ነው።
2. ከማህበሩ ጋር የሚዋሃደው ማህበር ጋር የሚደረገውን ድርድር የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባኤውን ስብሳቢ፣ ፀሀፊና የማህበሩን ፕሬዝዳንት ማካተት ይኖርበታል።

አን ቀጽ 27: <u>ስለማህበሩ መፍረስ</u>

1. ማህበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባኤ አባላት ማህበሩ እንዲፈርስ በ3/4ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው።
2. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የማህበሩ ፕሬዝዳንት የንብረት ቆጠራ /inventory/ ሰርቶ ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ ለበሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ያቀርባል።
3. ጠቅላላ ጉባኤው ማህበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ላይ የማህበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር ወይም የመንግስት አካል ሊያመለክት ይችላል።

አንቀጽ 28: <u>የመተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ የመተዳደርያ ደንብ በሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ባለሥልጣን ***<u>ከተመዘገበበት ቀን ዓ.ም</u>*** ጀምሮ የጸና ይሆናል።

የመስራች አባልት ስምና ፊርማ

አንቀጽ 3፡ የመስራቾች ዝርዝር

ተ.ቁ	ሙሉ ስም	ፊርማ
1	ዶ/ር አፀደ ሰለሞን ረታ	
2	ዶ/ር እስመለአለም ምህረቱ ተገኝ	
3	አቶ አስፋው መኩሪያ ይርጉ	
4	አቶ አፈወርቅ በዳዊ ሐሰን	
5	ዶ/ር ሰጠኝ ገበየሁ አንድሬ	
6	ወ/ሮ ማህሌት ዮሐንስ ስርጋዊ	
7	አቶ ደርበው ከበደ ኳልማዝ	
8	አቶ ሞገስ ጎበና ጅሩ	
9	ወ/ሮ ራውዳ ሰማን ጁቤር	